Washington State Health Care Authority

# የApple Health ማስፋፊያ ኖቬምበር 2023 ዌቢናር

## ተደጋግሞ የሚነሱ ጥያቄዎች

የ ስለፕሮግራሙን አጠቃላይ ሁኔታን ለማግኘት የApple Health ማስፋፊያ ብቁነት መረጃ ወረቀቱን ይመልከቱ። የሚከተሉት በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች በኖቬምበር 29፣ 2023 የባለድርሻ አካላት ዌቢናር የብቁነትን፣ የተሸፈኑ አገልግሎቶችንና ሌሎች የሚገኙ ፕሮግራሞችን አጠቃላይ ሁኔታ ያካፈሉ ጥያቄዎችን ይሸፍናል።

ዌቢናሩን ይመልከቱ | የማቅረቢያ ስላይዶች

የተተረጎሙ የዝግጅት አቀራረብ ስላይዶች: አማርኛ | አረብኛ | ካምቦዲያንኛ | ቻይንኛ | ሩሲያንኛ | ስፓኒሽኛ | ታጋሎግኛ | ዩክሬንኛ | ቬትናምኛ

## Apple Health ማስፋፊያ

### ደንበኞች ለሽፋን እንዴት ማመልከት ይችላሉ?

**ዕድሜያቸው 65 እና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች Washington Healthplanfinder ወይም በዋሽንግተን ኮኔክሽን (Washington Connection) በኩል ማመልከት ይችላሉ?**

- **ዕድሜያቸው 19-64 የሆኑ ግለሰቦች:**
  - **ኦንላይን**: ወደ Washington Healthplanfinder ይሂዱ - "አሁኑኑ ያመልክቱ" የሚለውን ቁልፍ ይምረጡ>
  - **የሞባይል መተግበሪያ:** የWAPlanfinder አፕልኬሽንን ያውርዱ - «ግባ»ን ይምረጡ ወይም «አካዎንት ይክፈቱ»።
  - **ስልክ**: ለWashington Healthplanfinder የደንበኞች ድጋፍ ማዕከል በ1-855-923-4633 ይደውሉ።
  - **ወረቀት**: የጤና እንክብካቤ ሽፋን (18-001P) ማመልከቻ ያስገቡ።
  - **በአካል**: የአካባቢ ሃብቶች ከተጨማሪ ክፍያ ነጻ በሆኑ መልኩ ለጤና ሽፋን እንዲያመለክቱ ሊያግዝዎት ይችላል።
    - የአካባቢ ቅበላ እገዛ

- **ዕድሜያቸው 65 እና ከዚያ በላይ የሆኑ ግለሰቦች፤**
  - **ኦንላይን**: ወደ ዋሽንግተን ግንኙነት ሂድ - "አሁኑኑ ያመልክቱ" የሚለውን ይምረጡ።
  - ወደ ዋሽንግተን ኮኔክሽን እንዴት እንደሚገቡ ይወቁ።
  - የብቁነት ግምገማዎን እንዴት ማጠናቀቅ እንደሚችሉ ይወቁ።
  - **ወረቀት**: ለአረጋውያን፣ ዓይነ ስውራን፣ የአካል ጉዳተኞች/የረጅም ጊዜ እንክብካቤ ሽፋን (HCA 18-005) ማመልከቻ ያስገቡ።
  - **ስልክ**: በ1-877-501-2233 በመደወል ማመልከቻ ይጠይቁ።
  - **በአካል**: የአካባቢዎን የማህበራዊና የጤና አገልግሎቶች መምሪያ (DSHS) ቢሮ ይጎብኙ።
    - ለአረጋውያን፣ ዓይነ-ስውራን ወይም የአካል ጉዳተኛ ሽፋን: DSHS የማህበረሰብ አገልግሎት ጽ/ቤት
    - ለረጅም ጊዜ አገልግሎቶችና ድጋፎች: የቤትና የማህበረሰብ አገልግሎት ቢሮ

**የደንበኛ አፕሊኬሽን መረጃ ለምን ያህል ጊዜ በአካዎንታቸው ውስጥ ይቀመጣል?**

የደንበኛ አፕልኬሽን መረጃ በቋሚነት በመተግበሪያ ስርዓቶች ውስጥ ይቆያል። አመልካቾች በማንኛውም ጊዜ መረጃቸውን ማደስ ወይም በአካዎንታቸው ላይ ለውጦችን ማድረግ ይችላሉ።

### ሰዎች ለApple Health ማስፋፍያ መቼ ማመልከት ይችላሉ?

ሰዎች ከስፕሪንግ 2024 ጀምሮ ለApple Health ማስፋፊያ ማመልከት ይችላሉ። ትክክለኛው ቀን በ Apple Health ማስፋፊያ ድረ-ገጽ ላይ እንደተገኘ ይጋራል። የሽፋን መጀመሪያው ቀን ጁላይ 1፣ 2024 ነው።

### ያላገቡና ሰነድ የሌላቸው እንደዚሁም አብረው የሚኖሩ ግለሰቦች ለApple Health ማስፋፊያ ሲያመለክቱ የተለየ ማመልከቻ ማስገባት አለባቸው?

ያላገቡና አብረው የሚኖሩ ግለሰቦች በአንድ ማመልከቻ ላይ መሆን አያስፈልጋቸውም እና የራሳቸውን ማመልከቻ ማቅረብ አለባቸው።

አብረው የሚኖሩ የተጋቡ ግለሰቦች በተመሳሳይ ማመልከቻ ላይ ማመልከት ይችላሉ።

## ሲያመለክቱ የሚያስፈልግዎ መረጃ

### ለሽፋን በሚያመለክቱበት ጊዜ ደንበኞች የገቢ ማረጋገጫ ማቅረብ አለባቸው?

በመጀመሪያው ማመልከቻ ሂደት የገቢ ማረጋገጫ አያስፈልግም። ደንበኞች የገቢ ማረጋገጫ እንዲያቀርቡ የሚጠይቅ ደብዳቤ ሊደርሳቸው ይችላል።

### ወቅታዊ ሰራተኞች ገቢያቸውን እንዴት ሪፖርት ማድረግ አለባቸው?

ግለሰቦች Washington Healthplanfinder በኩል በኦንላይን ላይ ሲያመለክቱ ስርዓቱ ከአሁኑ ወር ገቢ ይጠይቃል። በApple Health ማስፋፊያ ውስጥ የተመዘገቡ ደንበኞች ወርሃዊ ገቢያቸው $150 ዶላር ወይም ከዚያ በላይ ከተቀየረና ከአንድ ወር በላይ እንደሚቆይ ከተጠበቀው ሪፖርት ማድረግ አለባቸው። ገቢው ከቀነሰ ለተጨማሪ ቁጠባዎች ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።

ደንበኞች የሚለወጠውን ገቢ ሪፖርት ማድረግ የሚችሉባቸው ጥቂት መንገዶች አሉ:

- ሪፖርትአማካይወርሃዊ ገቢ. ይህ የደንበኛውን ዓመታዊ ገቢ ይወስዳልና ለ 12 ያካፍላል። ይህ አማካይ ወርሃዊ ገቢ ይሆናል።
- የአሁኑን ወር ትክክለኛ ገቢ ሪፖርት ያድርጉ። ደንበኞች ይህን ካደረጉ፣ ሲቀየር አዲስ የገቢ መጠን ሪፖርት ማድረግ ይችላሉ።

ገቢን ሲዘግቡ፣ አመልካቾች የሚከተለውን አካሄድ መምረጥ አለባቸው:

- አቅምን ከፍ ያደርገዋል።
- የሽፋኑን ቀጣይነት ይደግፋል።
- ሪፖርቱን ለመቀየር ይቀንሳል።

## ምዝገባ

### ከApple Health ዕቅዶች ውስጥ ለApple Health ማስፋፊያ ደንበኞች የሚቀርበው የትኛው ነው?

ምን ያህል ዕቅዶች ከዚህ አዲስ ፕሮግራም ጋር እንደሚተባበሩ አሁንም እየተጣራ ነው።

### ለApple Health ማስፋፊያ የቅበላ/ምዝገባ መጀመሪያ ቀን መቼ ነው?

ለApple Health ማስፋፊያ የመጀመሪያው የምዝገባ መጀመሪያ ቀን ጁላይ 1፣ 2024 ነው። ከጁላይ 1፣ 2024 በኋላ፣ ለሽፋን የተፈቀደላቸው ደንበኞች ባመለከቱበት ወር የመጀመሪያ ቀን ይመዘገባሉ።

### ብቁ የሆነና ለApple Health ማስፋፊያ ያመለከተ ሰው ሁሉ ይመዘገባል?

የጤና እንክብካቤ ባለስልጣን (HCA) Apple Health ማስፋፊያን ተግባራዊ ለማድረግ የገንዘብ ድጋፍ አግኝቷል። HCA በበጀት ውስንነት ምክንያት ብቁ የሆኑ ግለሰቦች ቁጥር ከሚገኙት ቦታዎች እንደሚበልጥ ይገምታል። በጥር መጨረሻ የምዝገባ ግምት ይኖረናል።

## ብቁነት እና ማረጋገጫ

### ለApple Health ማስፋፊያ ገቢ መቼ እና እንዴት ነው የሚያረጋግጡት?

በድህረ የብቃት ግምገማዎችና ገቢን የማረጋገጥ ሂደት ላይ መረጃን የሚያጋራ HCA መጪ የብቃት ዌቢናር ይይዛል።

### አንድ ግለሰብ በብዙ ሰዎች ቤተሰብ ውስጥ የሚኖር ከሆነ ምን ገቢ መቅረብ አለበት?

ዕድሜያቸው 65 እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ግለሰቦች:

- ብቁነት ግለሰቡ ወይም የትዳር ጓደኛቸው በሚያገኙት ወይም በሚደርሳቸው ገቢ ላይ የተመሰረተ ይሆናል። የአንድ ግለሰብ የግብር ማስመዝገቢያ ሁኔታ ዕድሜያቸው 65 እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ግለሰቦች የብቁነት ምክንያት አይደለም።

ዕድሜያቸው ከ19-64 ለሆኑ ግለሰቦች:

- ብቁነት ለሁሉም ጎልማሶችና ሁሉም ታዳጊዎች የግብር ተመላሽ እንዲያስገቡ የሚጠይቁ በቂ ገቢ ያላቸው የገቢ መረጃ ላይ የተመሰረተ ነው።

### ገቢ የሌላቸው ግለሰቦች ለሽፋን ማመልከት ይችላሉ?

ግለሰቦች ለሽፋን ሲያመለክቱ አሁን ያላቸውን ገቢ ሪፖርት ማድረግ አለባቸው። አንድ ግለሰብ በማመልከቻው ጊዜ ገቢ ከሌለው ዜሮ ገቢን ሪፖርት ማድረግ አለበት።

### ለአፕልከሽኑ ገቢን እንዴት ማስላት ይቻላል?

ገቢ በአሁኑ ጊዜ እንዴት ሪፖርት እንደሚደረግ ወይም እንደሚሰላ ላይ ምንም ለውጦች አይደረጉም። የመስመር ላይ አፕልከሽን የገቢ ዓይነቶችን ይጠይቃልና ገቢዎን ለማስላት ይረዳዎታል።

### በህጋዊ መንገድ የቀረቡ ሰዎች ለApple Health ማስፋፊያ ብቁ ይሆናሉ?

በህጋዊ መንገድ የቀረቡት የአምስት ዓመት ዝግድ ያላሟሉ ሰዎች በአሁኑ ጊዜ ለፌዴራል ድጎማ ብቁ ናቸው እና ለApple Health ማስፋፊያ ብቁ አይሆኑም።

## የተሸፈኑ አገልግሎቶች

### በApple Health ማስፋፊያ ስር ምን ዓይነት አገልግሎቶች ይሸፈናሉ?

የApple Health ማስፋፊያ የአካልና የባህሪ ጤና አገልግሎቶችን፣ የጥርስ ህክምና፣ የድንገተኛ ያልሆነ የህክምና መጓጓዣ እንደዚሁም የአስተርጓሚ አገልግሎቶችን ይሸፍናል። የረጅም ጊዜ አገልግሎቶችና ድጋፎች በApple Health ማስፋፊያ ስር አይሸፈኑም።

### በApple Health ማስፋፊያ ስር የጤና ቤት አገልግሎቶች ይገናኛሉ?

የጤና ቤት አገልግሎቶች በApple Health ማስፋፊያ ስር አይሸፈኑም። የመጀመሪያ ደረጃ እንክብካቤና እንክብካቤ ማስተባበር ግንኙነት በApple Health ማስፋፊያ ተመዝጋቢ ዕቅድ በኩል ይገኛል።

## ማዳረስ

### ለApple Health ማስፋፊያ ምን ዓይነት ማህበረሰብ ተኮር ድርጅቶች (CBO) ናቸው እየተሳተፉ ያሉት?

ተመዝጋቢ ሊሆኑ የሚችሉና በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚሳተፉ CBOs ዝርዝር ለማየት የመሪ ድርጅት ካርታውን ይመልከቱ። HCA በየወሩና በየሩብ ዓመቱ በሚደረጉ ስብሰባዎች ላይ ከባለድርሻ አካላትና አጋሮች ጋር በመላ ስቴቱ ይሳተፋልና በመዳረሻ ውስጥ በስፕሪንግ 2024 CBOs እንዲሳተፉ ለመጋበዝ ኮሙንኬሽኖች ይልካል።

## የደንበኛ መረጃ ግላዊነትና ጥበቃ

### HCA የኢሚግሬሽን ሁኔታ ዳታንና ሌሎች የግል ደንበኛን መረጃ እንዴት ይጠብቃል?

የApple Health ማስፋፊያ የደንበኞችን ማንነትና መረጃ ሚስጥራዊ ሆኖ መቆየቱን ለማረጋገጥ ያለውን የApple Health ግላዊነትና የጥበቃ ደረጃዎች ይጠቀማል። ለበለጠ መረጃ የHCA የግላዊነት ልምዶችን ይመልከቱ።

### HCA ማንኛውንም የደንበኛ መረጃ ለICE ወይም ለሌላ የፌደራል ወይም የህግ አስከባሪ ኤጀንሲዎች ያጋራል?

አያደለም። HCA የደንበኛ መረጃን ከማንኛውም የኢሚግሬሽን ኤጀንሲ ጋር አያጋራም፣ ICE ወይም ሌላ የፌዴራል ኤጀንሲዎችን ጨምሮ። ለApple Health ማስፋፊያ ብቁነት ከ የሕዝብ ክፍያ ሙከራነፃ ነው። የApple Health ማስፋፊያ ማመልከቻ የኢሚግሬሽን ሁኔታዎን ወይም ቋሚ ነዋሪ ወይም ዜጋ የመሆን እድሎችን እንዴት እንደሚጎዳ ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች ካሉዎት የኢሚግሬሽን ጠበቃን ያነጋግሩ።

## የሂሳብ አከፋፈልና ቅድመ-ፍቃድ

### ለApple Health ማስፋፊያ የሂሳብ አከፋፈልና የቅድሚያ ፈቃድ ሂደቶች ከሌሎች የApple Health ፕሮግራሞች የተለዩ ይሆናሉ?

Apple Health ማስፋፊያ የጥርስ ህክምናን ጨምሮ ነባሩን የApple Health የሂሳብ አከፋፈል መመሪያዎችንና የቅድሚያ ፈቃድ ሂደቶችን ለሁሉም አገልግሎቶች ይጠቀማል።

### የይገባኛል ጥያቄዎች ከዕቅዱ ይልቅ በቀጥታ ወደ Apple Health ይሄዳሉ?

ሁሉም የApple Health ማስፋፊያ አገልግሎቶች በApple Health ዕቅድ ይሸፈናሉ። ለApple Health ማስፋፊያ ምንም የApple Health ቀጥተኛ ክፍያ ለአገልግሎት የይገባኛል ጥያቄ ሂደት የለም።

## Apple Healthዕቅዶች

### በApple Health ማስፋፊያ ውስጥ የተመዘገቡ ደንበኞች በቀጥታ በApple Health ዕቅድም ይመዘገባሉ?

በApple Health ማስፋፊያ ውስጥ የተመዘገቡ ግለሰቦች ካሉት የApple Health ዕቅዶች ለመምረጥ ሊወዱት ይችላሉ። አንድ ደንበኛ ዕቅድ ካልመረጠ፣ አንዱ በካዎንትየዓቸው መሰረት ይመረጣል።

### በApple Health ነፍሰ ጡር ለሆኑ ሰቶች፣ከእርግዝና በኋላ ሽፋን (APC) ወይም ኤልየን ኢመርጄንሲ ሜድካል (AEM) ሽፋን በቀጥታ ነApple Health ማስፋፊያ ይመዘገባል?

በAEM ሽፋን የተመዘገቡ ደንበኞች በApple Health ማስፋፊያ ውስጥ አውቶማትካሊ በሆነ መንገድ ይመዘገባሉ።

በApple Health ነፍሰ ጡር ለሆኑ ሰቶች ወይም APC የተመዘገቡ ደንበኞች እንደተመዘገቡ ይቆያሉና ወደ Apple Health ማስፋፊያ አይሸጋገሩም።

### ደንበኞች ለApple Health ማስፋፊያ ብቁነታቸውን ካጡ ምን ይከሰታል?

የደንበኛ ሽፋን ከተቋረጠ እንደገና የመወሰን ሂደት ውስጥ ያልፋሉ።

## የአስተርጓሚ አገልግሎቶች

### የዌቢናርን የስፓኒሽኛ ትርጉም እንዴት ማግኘት እችላለሁ?

ዌቢናር በእንግሊዝኛና በስፓኒሽኛ የቀጥታ ዝግ መግለጫ ፅሁፎች (CC) ቀርቧል። የተዘጉ የመግለጫ ፅሁፎችን ቅጂ ለመጠየቅ ወደ ahexpansion@hca.wa.gov ኢሜይል ይላኩ።